የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፩ኛ ዓመት ቁጥር ፵፪
አዲስ አበባ ግንቦት ፭ ቀን ፪ሺ፲፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No. 42
ADDIS ABABA, 13th May, 2025

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፸፭/፪ሺ፲፯

የተፋሰሶች ከፍተኛ ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ……......................................ገጽ ፲፰ሺ፫፻፸፫

**Content**

Proclamation No. 1375/2025

Basins’ High Council Establishment Proclamation………....................Page 18373

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፸፭/፪ሺ፲፯

## የተቀናጀ ውሃ ሀብት አስተዳደር ማስፈጸሚያ የተፋሰሶች ከፍተኛ ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ

ኢትዮጵያ በአብዛኛው አካባቢዎቿ ተመጣጣኝ የሆነ ዝናብ የምታገኝና በርካታ የሀገር ውስጥና ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ባለቤት ብትሆንም ይህንን ሀብት የዜጎችን የላቀ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በአግባቡ ያልተጠቀመችበትና በቀጣይ በምታካሂደው ልማት የሕዝቦቿን ሁለንተናዊ ብልፅግና ለማረጋገጥ ወሳኝ በመሆኑ፤

የጋራ ዕቅድ፣ የተናበበ አተገባበር፣ ጠንካራ ክትትልና ግምገማ እንዲኖር በማድረግ በክልሎች ወይም በዘርፎች መካከል የሚከናወኑ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው የልማት ፕሮጀክቶች ውጤታማና ዘላቂነታቸውን ማረጋገጥ ተገቢ በመሆኑ፤

## PROCLAMATION No. 1375/2025

## BASINS’ HIGH COUNCIL FOR THE IMPLEMENTATION OF INTEGRATED WATER RESOURCE MANAGEMENT ESTABLISHMENT PROCLAMATION

**WHEREAS,** Ethiopia owns many domestic and transboundary rivers and enjoys even rainfalls in the majority of its regions, it has not utilized these resources to the optimal benefit of its citizens, and the proper utilization of its water sources is fundamental in its development endeavors to realize the overall prosperity of its peoples;

**WHEREAS,** it is appropriate to ensure the effectiveness and sustainability of water-related development projects that are of national importance and involve various regions or sectors through a joint plan, synergized execution, strong monitoring and evaluation system;

የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም፣ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን መገንባት፣ ዘላቂ ልማትን ማስፋፋት፣ የተፈጥሮ ሥነ ምህዳርን መጠበቅ፣ የውሃ ሀብት መጠንንና ጥራትን ማረጋገጥ፣ በአጠቃላይ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን መተግበር የሁሉንም አካላት ቀጥተኛ ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ፤

የተቀናጀ ውሃ ሀብት አስተዳደር ማስፈጸሚያ የተፋሰሶች ከፍተኛ ምክር ቤት መቋቋሙ አግባብነት ባላቸው አካላት ዘንድ የተቀናጀ ውጤታማ አመራርና አሰራር በመፍጠር የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር ፖሊሲን ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ ማድረግ የሚያስችል በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ “የተፋሰሶች ከፍተኛ ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፸፭/፪ሺ፲፯” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **“ተፋሰስ”** ማለት ወደ አንድ መልክዓ ምድራዊ አቅጣጫ የሚፈሱ የገፀ ምድርና በዚያው ትይዩ የሚገኙ የከርሰ ምድር ውሃዎች የሚያካልሉት አካባቢ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ ስር የተጠቀሱት ናቸው፤

**WHEREAS,** building a green economy resilient to climate change, expanding sustainable development, protecting the natural ecosystem, ensuring the quantity and quality of water resources, and generally, implementing integrated water resources management requires the direct participation of all stakeholders;

**WHEREAS,** recognizing that establishing Basins’ High Council for the Implementation of Integrated Water Resources Management can ensure the full implementation of Ethiopian water resources management policy by introducing effective and synergized governance and working mechanisms among relevant actors;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Article (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

## 1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as the “Basins’ High Council Establishment Proclamation No. 1375/2025.”

## 2. <u>Definitions</u>

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ **“Basin”** means a geographical area, described by the water system's watershed limits, including surface and underground water flowing into a common terminus, and shall include those specified under Article 3 of this Proclamation;

፪/ **“ክልል”** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፵፯ መሰረት የተቋቋመ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ መስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፫/ **“የከርሰ ምድር ውሃ”** ማለት ከመሬት ገጽ በታች የሚገኝ ውሃ ማለት ነው፡፡

፬/ **“የገጸ ምድር ውሃ”** ማለት የረጋ ወይም የሚፈስ በመሬት ላይ የሚገኝ ውሃ ነው፡፡

፭/ **“ምክር ቤት”** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተቋቋመው የተቀናጀ ውሃ ሀብት አስተዳደር ማስፈጸሚያ የተፋሰሶች ከፍተኛ ምክር ቤት ነው፤

፮/ **“ሚኒስቴር”** ማለት የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ነው፤

፯/ **“ባለድርሻ አካል”** ማለት በተፋሰስ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደት ይሁነኝ ብሎም ሆነ በአጋጣሚ የሚሳተፍ ወይም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ጥቅሙ የሚነካ ማንኛውም ሰው ነው፤

፰/ **“የውሃ ሀብት”** ማለት መጠንና ጥራትን ባካተተ ሁኔታ በተፋሰሱ ውስጥ የሚገኝ የገፀ ምድር ወይም የከርሰ ምድር ውሃ ሲሆን የውሃ ስነ-ምህዳርንና ረግረጋማ መሬትን ያጠቃልላል፤

፱/ **“የውሃ ሀብት አስተዳደር”** ማለት የውሃ ሀብት ማልማትን፣ መጠቀምን፣ መንከባከብን፣ መጠበቅንና መቆጣጠርን የሚመለከቱ ተግባራትን ያካትታል፤

2/ **“Regional State”** means any regional state established according to Article 47 of the FDRE Constitution and includes the Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

3/ **“Groundwater”** means water below the surface of the earth.

4/ **“Surface Water”** means water that is found on the surface of the earth, whether standing or flowing.

5/ **“The Council”** means Basins’ High Council for the Implementation of Integrated Water Resources Management established pursuant to Sub Article (1) of Article 5 of this Proclamation;

6/ “Ministry” means the Ministry of Water and Energy;

7/ **“Stakeholder”** means any person who is intentionally or incidentally involved in, or directly or indirectly affected by, water resources management in a basin;

8/ **“Water Resources”** means the availability, both in quantity and quality, of surface and groundwater in a river basin including aquatic ecosystems and wetlands;

9/ **“Water Resource Management”** means activities that include water resources development, utilization, conservation, protection, and control;

፲/ **“የተቀናጀ ውሃ ሀብት አስተዳደር”** ማለት ውሃ እንደ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ሀብትነቱ በተፋሰስ ውስጥ ካሉ የተለያዩ አጠቃቀሞች ጋር ሙሉ በሙሉ የተጣጣመ ሆኖ ሚዛናዊ እና ዘላቂነት ያለው የውሃ ሀብት ልማት እንዲኖር የሚያስችል ስርዓት ነው፤

፲፩/ **“የውሃ ምደባ”** ማለት የተፋሰስን የውሃ ሀብት በውሃ የመጠቀም ፈቃድ ስርዓትን በመተግበር ለልዩ ልዩ አጠቃቀሞች እና ተጠቃሚዎች ማከፋፈል ነው፤

፲፪/ **“የውሃ አጠቃቀም”** ማለት ውሃን ለመጠጥ፣ ለመስኖ ወይም ለእርሻ፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለኃይል ምንጭነት፣ ለትራንስፖርት፣ ለቱሪዝም፣ ለእንስሳት እርባታ፣ ለአሣ ማስገር፣ ለማዕድን ልማት ወይም ለሌሎች ግልጋሎቶች መጠቀም ነው፤

፲፫/ **“የተፋሰስ ዕቅድ”** ማለት የውሃ ሀብትን ማዕከል በማድረግ በባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የሚዘጋጅና በተሰጣቸውም ሥልጣንና ተግባር መሰረት ፍትሃዊና ዘላቂነትን በሚያረጋግጥ ሁኔታ የሚተገበር የረዥም ጊዜ ራዕይ ያለው ሁሉን አቀፍ የተቀናጀ ስትራቴጂክ ዕቅድ ነው፤

፲፬/ **“ከፍተኛ የልማት ፕሮጀክት”** ማለት በባለድርሻ አካል የሚከናወን በዓይነቱ፣ በመጠኑ፣ በዋጋው፣ በውስብስብነቱ ወይም በግንባታ በሚወስደው ጊዜ የተለየ ፕሮጀክት ሲሆን በተፋሰሱ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር ነው፤

10/ **“Integrated Water Resources Management”** means an arrangement for balanced and sustainable development of water, as an economic, social, and environmental resource, reconciling, fully, its various uses within a basin;

11/ **“Water Allocation”** means a system of sharing the water available in a basin among various uses and users according to water use permits;

12/ **“Water Use”** means the use of water for drinking, irrigation, industry, power generation, transport, tourism, animal husbandary, fishing, mining and uses of water for other purposes;

13/ **“Basin Plan”** means strategic water resource planning with long-term vision prepared by stakeholders to be implemented by their respective powers and responsibilities to guarantee equity and sustainability in water resource uses;

14/ **“Major Development Project”** means a development project implemented by a relevant stakeholder that is unique in its type, size, cost, complexity, or duration of implementation while having direct or indirect, and positive or negative impact on a basin;

፲፭/ **"ከፍተኛ የውሃ ነክ ሥራ"** ማለት የውሃ ሀብትን ለመጠቀም ወይም ውሃ ነክ አደጋዎችን ለመከላከል የተገነባ ወይም የሚገነባ በውሃ ሀብቱ መጠን፣ ጥራትና ፍሰት ላይ ጉልህ ለውጥ የሚያመጣ ተግባርን ያጠቃልላል፤

፲፮/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፯/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

## ፫. ስለ ኢትዮጵያ ተፋሰሶች

በኢትዮጵያ የሚገኙ ዋና ዋና ተፋሰሶች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው፡-

፩/ የአባይ ተፋሰስ፤

፪/ የአይሻ ተፋሰስ፤

፫/ የአዋሽ ተፋሰስ፤

፬/ የባሮ አኮቦ ተፋሰስ፤

፭/ የደናኪል ተፋሰስ፤

፮/ የገናሌ ዳዋ ተፋሰስ፤

፯/ የመረብ ተፋሰስ፤

፰/ የኦጋዴን ተፋሰስ፤

፱/ የኦሞ ጊቤ ተፋሰስ፤

፲/ የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ፤

፲፩/ የተከዜ ተፋሰስ፤ እና

፲፪/ የዋቢ ሸበሌ ተፋሰስ፡፡

## ፬. የተቀናጀ ውሃ ሀብት አስተዳደር

የተቀናጀ ውሃ ሀብት አስተዳደር አተገባበር በዋናነት የተፋሰስ ዕቅድን፣ የተፋሰስ መረጃ ስርዓትን፣ የውሃ ሀብት ምደባና አጠቃቀምንና አግባብነት ያላቸው አካላትን ቅንጅትን መሰረት ያደረገ ይሆናል፡፡

፩/ የተፋሰስ ዕቅድ የሚከተሉትን መሰረታዊ ጉዳዮች ማካተት ይኖርበታል፡-

15/ **"Major Water-related Work"** means an already built construction or a construction to be built with a view to utilize a water resource or to prevent water related dangers which has a significant impact on the quantity and quality of the water resource;

16/ **"Person"** means any natural or juridical person;

17/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Ethiopian Basins

The following are the main basins of Ethiopia:

1/ The Abbay Basin;

2/ The Aisha Basin;

3/ The Awash Basin;

4/ The Baro-Akobo Basin;

5/ The Danakil Basin;

6/ The Genale-Dawa Basin;

7/ The Mereb Basin;

8/ The Ogaden Basin;

9/ The Omo-Ghibe Basin;

10/ The Rift Valley Lakes Basin;

11/ The Tekeze Basin; and

12/ The Wabe-Shebelle Basin.

## 4. Integrated Water Resource Management

The implementation of integrated water resource management shall be based mainly on a basin plan, basin information system, water allocation and use, and integration of stakeholders.

1/ A basin plan shall include the following basic issues:

ሀ) የተፋሰሱን የውሃ ሀብት፤

ለ) የተፋሰሱን እንክብካቤ ሁኔታ፤

ሐ) በውሃ ሀብቱ ላይ ከፍተኛ ጫና የሚያሳድሩ ሁኔታዎችን፤

መ) በተፋሰሱ ውስጥ ያለውን የውሃ አጠቃቀም ደረጃ የሚያሳይ አኃዛዊ መግለጫን፤

ሠ) የተፋሰሱን የወደፊት ሁኔታ ሊያሳይ የሚችል ትንተናን፤

ረ) የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደት አተገባበርን ዕውን ለማድረግ የሚረዱ ስትራቴጂዎችን፤ እና

ሰ) ዕቅዱን የሚተገብሩ አካላት የድርጊት መርሃ-ግብር፣ የሚያስፈልገውን ሀብት፣ በጀት እና የበጀት ምንጭን ጨምሮ ዕቅዱን ተግባራዊ የማድረጊያ ዘዴዎችን፡፡

፪/ የተፋሰስ መረጃ ስርዓት ቢያንስ የሚከተሉትን ቁልፍ አመላካቾች ማካተት ይኖርበታል፡-

ሀ) የተፋሰሱን የውሃ ሀብት መጠንና ጥራት፤

ለ) የተፋሰሱን የውሃ የተፈጥሮ ሥነ ምህዳር፤

ሐ) በተፋሰሱ ውስጥ ያለውን የውሃ ፍላጎት፤

መ) ነባርና ለወደፊቱ የታቀዱ ዋና ዋና መሰረተ ልማቶችን፤

ሠ) በውሃ ሀብቱ ላይ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ዋና ዋና ጣልቃ ገብ ስራዎችን ወይም ፕሮጀክቶችን፤

ረ) በሥራ ላይ ያለውን የውሃ አጠቃቀም፤ እና

a) Basin’s water resource;

b) Basin’s management situation;

c) Factors that overburdened the water resource;

d) Numerical description of the level of water use within the basin;

e) Analysis that forecasts the future situation of the basin;

f) Strategies that help to realize the implementation of integrated water resources management; and

g) Action plan, budget and budget source, and ways of execution for respective actors who are responsible for the implementation of the basin plan.

2/ A basin information system shall at least include the following key indicators:

a) Basin’s water resource quantity and quality;

b) Basin’s aquatic ecosystem;

c) Water demands within the basin;

d) Existing and planned main infrastructures;

e) Main intervening activities or projects that can impact the water resource;

f) Implemented water use; and

ሰ) የተፋሰሱን ባለድርሻ አካላት፡፡

፫/ የውሃ ምደባና አጠቃቀም፡-

ሀ) የውሃ ምደባ በተፋሰስ ደረጃ ተግባራዊ የሚደረገው የውሃ አለኝታን፣ የውሃ ተጠቃሚን፣ የውሃ አጠቃቀምንና ወቅትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ነው፤

ለ) የውሃ ምደባ ስርዓት ማህበራዊ ፍትህን፣ ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታንና አካባቢያዊ ዘላቂነትን በሚያረጋግጥ አግባብ ይከናወናል፤

ሐ) በውሃ ለመጠቀም ወይም ውሃ ነክ ሥራዎች ለመስራት የሚያስችል ፍቃድ ከተቀናጀ ውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደት ጋር የተጣጣመ ይሆናል፡፡

፬/ የባለድርሻ አካላት ቅንጅት፡-

ሀ) ባለድርሻ አካላት በተፋሰስ ዕቅድ ዝግጅት፣ ትግበራ፣ ክትትልና ግምገማ ላይ መሳተፍ አለባቸው፤

ለ) በተፋሰስ ውስጥ የሚከናወኑ ከውሃ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን ከተፋሰስ ዕቅዱ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ከባለድርሻ አካላት በጋራ ያረጋግጣሉ፤

ሐ) የተቀናጀ መረጃ ስርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ ማንኛውም ባለድርሻ አካል ከውሃ ሀብት ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎችን ለሚኒስቴሩ የመስጠትና ሚኒስቴሩ በሚያወጣው የመረጃ ልውውጥ ፕሮቶኮል መሰረት የመተግበር ግዴታ አለበት፡፡

g) Stakeholder of the basin.

3/ Water allocation and use:

a) At the basin level, water allocation shall be made subject to water security, water users, water use, and water season;

b) Water allocation shall be made in a manner that ensures social justice, economic benefit, and environmental sustainability;

c) A permit for water uses or water-related works shall conform with the integrated water resource management process.

4/ Stakeholders integration:

a) Stakeholders shall participate in the preparation, implementation, monitoring and evaluation of a basin plan;

b) Stakeholders shall jointly ensure that water-related programs or projects to be implemented within the basin are in harmony with the basin plan;

c) To realize an integrated basin information system, every stakeholder is under obligation to provide the Ministry with water-related information and to act as per the information exchange protocol to be issued by the Ministry.

## ፭. ስለ ምክር ቤቱ መቋቋም

፩/ የተቀናጀ ውሃ ሀብት አስተዳደር ማስፈጸሚያ የተፋሰሶች ከፍተኛ ምክር ቤት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ምክር ቤቱ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

## ፮. ዓላማ

የምክር ቤቱ አጠቃላይ ዓላማ የውሃ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ፍትሃዊነትና አሳታፊነትን ባረጋገጠ ሁኔታ እንዲሁም የውሃ ሥነ-ምህዳርን ዘላቂነት በጠበቀ መልኩ እንዲሆን የተቀናጀ ውሃ ሀብት አስተዳደር በሀገሪቱ በወጥነት ተግባራዊ እንዲደረግ ስትራቴጂያዊ አመራር መስጠት ነው፡፡

## ፯. ስለ ምክር ቤቱ አባላት

፩/ ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር-----------------------------------------------ሰብሳቢ

ለ) የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር----------------------------------ም/ሰብሳቢ

ሐ) የክልል ርዕሰ መስተዳደሮች--------------------------------------------------አባል

መ) የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባዎች-----------አባል

ሠ) የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር----------------------------------------------አባል

ረ) የመስኖና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር ሚኒስትር---------------------------አባል

ሰ) የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር---------------------------አባል

ሸ) የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር-------------------------------------------------አባል

## 5. Establishment

1/ The Basins' High Council for the Implementation of Integrated Water Resource Management is hereby established.

2/ The Council shall be accountable to the Prime Minister.

## 6. Objective

The overall objectives of the Council shall be to give strategic leadership regarding the implementation of integrated water resources management to ensure that basins' water resources are developed and utilized in an equitable and participatory manner, and without compromising the sustainability of the aquatic ecosystems.

## 7. Members of the Council

1/ The Council shall have the following members:

a) Deputy Prime Minister……………………….......................Chairperson;

b) Minister of the Ministry of Water and Energy………..Vice Chairperson

c) Presidents of the Regional States……………………….Member

d) Mayors of the Addis Ababa and Dire Dawa City Administration…………………………………………..Member

e) Minister of the Ministry of Agriculture…………………Member

f) Minister of the Ministry Irrigation and Low Land.……………..Member

g) Minister of the Ministry of Plan and Development……………....Member

h) Minister of the Ministry of Finance……………………..Member

ቀ) የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር-------------------------------------------አባል

በ) የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር---------------------------አባል

ተ) የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር-------------------------------------------------አባል

ቸ) የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ሚኒስትር--------------አባል

ኀ) የማዕድን ሚኒስቴር ሚኒስትር-----------------------------------------------አባል

ነ) የሰላም ሚኒስቴር ሚኒስትር-------------------------------------------------አባል

ኘ) የቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር----------------------------------------------አባል

አ) የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር-------------------------------------------አባል

ከ) የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር---------------------------አባል

ኸ) የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር-------------------------አባል፡፡

፪/ ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አዲስ የምክር ቤት አባል መጨመርና ለተወሰኑ ጉዳዮች የተቋም የበላይ ኃላፊዎች ወይም ሌሎች አካላት በምክር ቤቱ ስብሰባ እንዲሳተፉ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፰. <u>የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ረገድ በባለድርሻ አካላት መካከል የተጠናከረ ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን ማረጋገጥ የሚያስችል ስርዓት የመፍጠር እንዲሁም ተግባራዊነቱንም የማረጋገጥ፤

i) Minister of the Ministry Industry ……………………………………Member

j) Minister of the Ministry of Urban and Infrastructure…………………………………………………..Member

k) Minister of the Ministry of Health………………………Member

l) Minister of the Ministry of Transport and Logistics……………….Member

m) Minister of the Ministry of Mine ………………………………Member

n) Minister of the Ministry of Peace ……………………………Member

o) Minister of the Ministry of Tourism ……………………………… Member

p) Minister of Ministry of Foreign affairs………………………Member

q) Ministry of Women and Social Affairs…………………….Member

r) Commissioner of the Commission of Disaster Risk Management…………………………………….... Member.

2/ Where it deems necessary, the Council may add new members and based on its specific agenda, may cause relevant government officials or any other actors to attend its meeting.

8. **<u>Powers and Duties of the Council</u>**

The Council has the following powers and duties:

1/ Provide policy guidance and planning oversight to ensure a high level of coordination among stakeholders for the implementation of integrated water resources management in basins;

፪/ የተፋሰስ ዕቅድ እንዲዘጋጅ አመራር የመስጠት፣ መርምሮ የማጽደቅ፣ የጸደቀውን ዕቅድ በተፋሰሱ ውስጥ አግባብ ባላቸው አካላት ሁሉ በቅንጅት እየተተገበረ መሆኑን የመከታተል፣ በአፈጻጸም ሂደት ለታዩ ጉዳዮች ውሳኔ የመስጠት፤

፫/ ከፍተኛ የልማት ፕሮጀክቶች ከተፋሰስ ዕቅድ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን የማረጋገጥ፤

፬/ በተፋሰስ ውስጥ የከፍተኛ የውሃ ነክ ሥራ ግንባታንና የቅደም ተከተልን አግባብነት መርምሮ የመወሰን፤

፭/ ከአንድ ተፋሰስ ወደ ሌላ ተፋሰስ የሚደረግ የውሃ ሽግግርን አስፈላጊነት መርምሮ የመወሰን፤

፮/ የውሃ ምደባ ፍትሃዊነትን መርምሮ የመወሰን፤

፯/ በተፋሰሱ የውሃ ሀብት አጠቃቀም ክፍያ ተመን ጥናትን መርምሮ የማጽደቅ፤

፰/ ከውሃ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ በክልሎች መካከል የሚነሳ አለመግባባትን በመመርመር መፍትሄ የመስጠት፤

፱/ በየተፋሰሱ ከውሃ አጠቃቀምና አስተዳደር ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን መርምሮ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የምክር ቤት አባላትን የያዘ ኮሚቴ የማቋቋም፤ እንዲሁም የቀረበ የውሳኔ ሀሳብን መርምሮ የማጽደቅ፤

፲/ ምክር ቤቱ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን ምክረ ሀሳብ የሚያቀርብ የቴክኒክ ኮሚቴ የማቋቋም፡፡

2/ Give leadership for the preparation of the basin plan, examine and approve the same, monitor the implementation of the approved basin plan by stakeholders in an integrated manner, and decide on issues that arise during implementation;

3/ Ensure planned major development projects conform with a basin plan;

4/ Examine and decide on the appropriateness prioritization of constructing major water works in the basin;

5/ Examine and decide on the appropriateness of the transfer of water resources from one basin to another;

6/ Examine and decide on the equitability of water allocation;

7/ Examine and approve a proposal on the rate of water charges to be paid by water users in the basin;

8/ Examine and provide a solution for a dispute between regions regarding water use;

9/ Establish a committee composed of members of the council that study and provide a recommendation on issues related to water use and administration in the basin and examine and approve the recommendation;

10/ When the Council finds it necessary, it may establish a technic committee that provides a recommendation.

**፱. ስለ ምክር ቤቱ ስብሰባ**

፩/ ምክር ቤቱ በዓመት ቢያንስ ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፣ ሆኖም ግን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሰብሳቢው በራሱ አነሳሽነት ወይም ተፋሰስን ከሚጋሩ ክልሎች መካከል ቢያንስ በአንዱ ጥያቄ ከቀረበ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፪/ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የምክር ቤቱ አባላት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፡፡

፫/ ምክር ቤቱ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፣ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሃሳብ የምክር ቤቱ የውሳኔ ሆኖ ያልፋል፡፡

፬/ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢው የምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል፡፡

፭/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲. የምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት**

ሚኒስቴሩ የምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል፡፡

**፲፩. የሴክሬተሪያቱ ተግባርና ኃላፊነት**

ሴክሬተሪያቱ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩/ የምክር ቤቱን የመወያያ አጀንዳዎችን ይቀርጻል፤ ለምክር ቤቱ ሰብሳቢ ያቀርባል፤

**9. Meetings of the Council**

1/ The Council shall hold regular meetings at least twice a year; provided, however, that the chairperson may, on his own initiative or upon the request of one of the regions which share a basin, call an extraordinary meeting to be held at any time.

2/ There shall be a quorum where more than half of the members of the Council are present at a meeting.

3/ The Council shall pass decisions by majority vote; in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote.

4/ In the absence of the chairperson, the vice chairperson shall preside over the meetings of the Council.

5/ Notwithstanding the provisions of this Article, adopt its own rules of meeting procedure.

**10. Secretariat of the Council**

The Ministry shall serve as the Secretariat of the Council.

**11. Duties and Responsibilities of the Secretariat**

The Secretariat shall have the following duties and responsibilities:

1/ Propose agenda items and submit the same to the Council;

፪/ የምክር ቤቱን የስብሰባ ቃለ-ጉባዔ ይይዛል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያደርሳል፣ ከኮሚቴዎች የሚመጣን ሪፖርት ተቀብሎ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤ ሌሎች ምክር ቤቱን የሚመለከቱ ሰነዶችን ያደራጃል፤

፫/ በምክር ቤቱ የተሰጠ ውሳኔ አፈጻጸምን በመከታተል ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፤

፬/ የምክር ቤቱን እንቅስቃሴ እና ውሳኔዎች በተመለከተ የህዝብ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ተግባራትን ያከናውናል፤

፭/ በምክር ቤቱ የሚሰጡትን ተጨማሪ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፲፪. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ አፈጻጸም በተመለከተ ከምክር ቤቱ ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት።

## ፲፫. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲፬. ስለተሻሩና ተፈጻሚነት ስለሌላቸው ሕጎች

፩/ የተፋሰስ ምክር ቤቶችና ባለሥልጣናት አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፬/፩ሺ፱፻፺፱ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ጉዳዮች ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሰራር ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

2/ Record the minutes of the Council, deliver the same to concerned bodies, receive reports from committees, submit them to the Council, and file other documents of the Council;

3/ Follow up on the implementation of the decision of the Council and report its execution to the Council;

4/ Perform public relations and communication activities regarding the undertakings and decisions of the Council;

5/ Carry out other activities assigned to it by the Council.

## 12. Duty to Cooperate

Every person has the duty to cooperate with the Council in the implementation of this Proclamation.

## 13. Power to Issue Regulation and Directive

1/ The Council of Ministers may issue the necessary Regulations to implement this Proclamation.

2/ The Ministry may issue Directives necessary for the implementation of this Proclamation.

## 14. Repealed and Inapplicable Laws

1/ River Basin Councils and Authorities Proclamation No.534/2007 is hereby repealed.

2/ No law shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for in this Proclamation.

**፲፭. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፭ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዘዳንት**

**15. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force upon its publication in the Federal Negarit Gazete.

**Done at Addis Ababa, On this 13th day of May, 2025**

**TAYE ATSKE SELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**